# ፖለቲካዊ መግባባት

# እና

# 18 የፖልቶክ ታዳሚዎች

## ጥያቄና መልስ

*October 2013*

አዘጋጅ፡- ያዬ አበበ
አሪዞና ፥ አሜሪካ

Email: yaye.abebe@gmail.com Phone: 602-380-8318

# መግቢያ

- **ይህ ጥያቄ እና መልስ ከ18 የፓልቶክ ታዳሚዎች ጋር ስለ ፓለቲካዊ መግባባት ("ብሄራዊ መግባባት") የተደረገ ነው።**



ያዬ አበበ

- ጥያቄ እና መልስ የተደረገበት ጊዜ ከSeptember 16-20, 2013 ሲሆን ፡ ጠያቂ አቶ ያዬ አበበ ነው (Paltalk nick name: Beruhan)።

- የዚህ ጥያቄ እና መልስ **አላማ** የፓልቶክ ታዳሚዎች ስለ ፓለቲካዊ መግባበት ያለቸውን ግንዛቤ ለማሰስ ሲሆን ፡ በተጨማሪ የአሰሳውን ውጤት በመጠቀም ስለ ፓለቲካዊ መግባባት በዲያስፓራ መወያያ መድረኮችና ሚዲያዎች ግንዛቤ የሚያስጨብጥና ጥልቀት ያለው የፓለቲካ ውይይት የሚፈጥር ጥንስስ ለመጀመር ነው።

- ይህ ጥያቄና መልስ አሰሳዊ እንጂ ስታትስቲካል አይደለም።

- በጥያቄ እና መልሱ ወቅት ተጠያቂዎች ያልመልሱዋቸው ወይም የዘለሉዋቸው ጥያቄዎች አሉ። ጥያቄዎቹ የተዘለሉበት ምክንያት ተጠያቂዎች ትኩረት የስጡት ለሌሎች ጥያቄዎች በመሆኑና ከጊዜ ገደብ ጭምር ነው።

- በጥያቄና መልሱ ላይ የተሳተፉትን ወገኖቼን ሁሉ ስለ ትብብራቸውና ቅንነታቸው አምሰግናለሁ።

\- ያዬ አበበ

# ማውጫ


**አስራ ሁለት ጥያቄዎች** ______ ገጽ 4

**መልስ**

**የኢህአዴግ ደጋፊዎች**

ደጋፊ 1 ______ 5

ደጋፊ 2 ______ 7

ደጋፊ 3 ______ 8

ደጋፊ 4 ______ 11

ደጋፊ 5 ______ 13

ደጋፊ 6 ______ 15

**የህጋዊ ተቃዋሚ ደጋፊዎች**

ተቃዋሚ 1 ______ 17

ተቃዋሚ 2 ______ 19

ተቃዋሚ 3 ______ 21

ተቃዋሚ 4 ______ 23

ተቃዋሚ 5 ______ 25

ተቃዋሚ 6 ______ 27

**ለዘብተኞች** *('ለዘብተኞች' ማለት ከፓርቲ ደጋፊነት ይልቅ በመርህ ላይ ሚያተኩሩ ናቸው።)*

ለዘብተኛ 1 ______ 29

ለዘብተኛ 2 ______ 31

ለዘብተኛ 3 ______ 33

ለዘብተኛ 4 ______ 35

# አስራ ሁለት ጥያቄዎች

*አጠቃላይ ጥያቄዎች*

1. በዲያስፓራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?
2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?
3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

*የመግባባት ጥያቄዎች*

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

*ዲያስፓራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች*

6. የምርጫ 2002 99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፓለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፓራ ላይ ምን አይነ ት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

*የተለያዩ ሰዎች ውጠርት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ንድፈ-ሃሳቦች*

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?
9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፓሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?
10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፓሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገብር ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

*የእውቅና ጥያቄ*

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

*የመዝጊያ ጥያቄ*

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

# መልስ፡- የኢህአዴግ ደጋፊዎች

## ደጋፊ 1

***አጠቃላይ ጥያቄዎች***

1. በዲያስፓራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?

   **መልስ፡-** *ውይይት አልተደረገም።*

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?

   **መልስ፡-** *አዎ። የፓለቲካ ፓርቲዎች የስልጣን ጥመኝነት ፤ አመራሮች የውጥረቱ ተጫዋቾች ናቸው።*

3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

   **መልስ፡-** *የለም። ከዚህ በፊት የነበረ የፓለቲካ ጉዞ ፣ በብሄር ጉዳይ ላይ ያለመተማመን ፣ ሰዉ ሁሉ የተወለደበትን ብሄር ስለሚያስቀድም ብሄሩን ያስቀድማልና።*

***የመግባባት ጥያቄዎች***

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፡-** *እድሜውን ለማራዘም ፤ ተቃዋሚዎች እንዳይተማመኑ ይፈልጋል። እርስ በርሳቸው ካላቸው ልዩነት የተነሳ ተቃዋሚዎች በህዝቦች አለመደገፋቸው ለኢህአዴግ ጠቅሞታል።*

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፡-** *ኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰብ አገር መሆኗን መቀበል አለባቸው ፤ ወደ አሃዳዊ መንግስት መመለስ አይቻልም። ከኢህአዴግ ጥሩውን መውሰድ።*

***ዲያስፓራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች***

6. የምርጫ 2002 99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

   **መልስ፡-** *ለተወሰነ ጊዜ የብር ማሰባሰቢያ ሆኖ ነበር። አሁን ያለው ትውልድ እና የፓለቲካ ድርጅቶች መካከል ክፍተት አለ።*

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፓለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፓራ ላይ ምን አይነ ት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

**መልስ፡-** *ኢህአዴግ ውስጥ ያለ ሁሉ ኢህአዴግን ወዶ ሳይሆን አማራጭ አጥቶ ነው። የኢሳት ሚና ፡ ሚዛናዊ ካልሆነ ተቀባይነት አይኖረውም።*

***የተለያዩ ሰዎች ውጥረት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ንድፈ-ሃሳቦች***

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *ህዝብ ያልተቀበለውን ማንፌስቶ ህዝብ ሊወያይወት ይገባል። ማንፌስቶ ነው ወይስ አፈጻጸም ነው? የህዝብ እይታ መታየት አለበት። ጥያቄው ከህዝብ መሆን አለበት። የፓለቲካ ፓርቲዎችን እንደ ጠላት ሳይሆን እንደ ኢጋር ማየት አለበት። ማንፌስቶ ከሆነ ችግሩ ፡ የህዝብ ጥያቄ መሆን አለበት።*

9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፓሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *እንደ ምኞት ሊሆን ይችላል። እንደ አገር ሊሆን አይችልም። የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች የመንግስት ሰራተኞች ናቸው። ኢህአዴግ ፈርሶ ኢህአዴግ ደካማ ነው ማለት ይፈልጋሉ።*

10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፓሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገብር ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

    **መልስ፡-** *ተቃዋሚ ፓርቲዎችም የኢህአዴግን ጥንካራ ጎን መደገፍ ፤ ኢህአዴግም የተቃዋሚዎችን ጠንካራ ጎን መደገፍ አለባቸው። የፓለቲካ ባህላችን ሌሎች ፓርቲዎችን እንደጠላት ነው የምናየው።*

***የእውቅና ጥያቄ***

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

    **መልስ፡-** *አልሰጡም ፤ እንዲያውም ደርግ ጥሩ ነው ብለው ሚያምኑ አሉ። መስዋዕትነቱ ከሁሉም ብሄር የተከፈለ ነው። ኢህአዴግ ደርግን በማስወገዱ እንደ ጥፋት የሚያዩ አሉ።*

***የመዝጊያ ጥያቄ***

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

    **መልስ፡-** *መልስ የለም*

# ደጋፊ 2

*አጠቃላይ ጥያቄዎች*

1. በዲያስፓራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?

   **መልስ፡-** *ስለ ብሄራዊ መግባባት ሰምቼ አላቅም። ገለልተኛ ሆኖ ለማስማማት የሰማሁት ነገር የለም።*

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?

   **መልስ፡-** *ከኢትዮጵያ ከወጣሁ ብዙ ጊዜ ስለሆነኝ አስተያየት መመስረት አልችልም።*

3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

   **መልስ፡-** *መግባባት ያለ አይመስለኝም። ልዩ ልዩ ክፍሎች እገባለሁ። ለማግባባት እሞክራለሁ። የጥላቻ ንግግር ይበዛል። እኛ አንድ ህዝብ ነን።*

*የመግባባት ጥያቄዎች*

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፡-** *እስረኞች ይፈቱ ባይ ነኝ። ስለጻፉ ነው የታሰሩት።*

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፡-** *ውይይት ያስፈልጋል። ደጋፊዎች እና ተቃዋሚዎች ቁጭ ብለው መወያየት አለባቸው። ውይይቱ ላይ የሚለጠፍ "ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ነን" የሚል መፈክር መጻፍና መለጠፍ እፈልጋለሁ።*

*ዲያስፓራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች*

6. የምርጫ 2002 99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

   **መልስ፡-** *መልስ የለም*

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፓለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፓራ ላይ ምን አይነ ት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

   **መልስ፡-** *መልስ የለም*

*የተለያዩ ሰዎች ውጥርት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ንድፈ-ሃሳቦች*

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *መልስ የለም*

9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፓሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *መልስ የለም*

10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፓሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገብር ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *መልስ የለም*

*የእውቅና ጥያቄ*

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

   **መልስ፡-** *ሲቃወሙም ሰምቼ አላቅም ፤ ሲያከብሩም ሰምቼ አላቅም። ቸልተኞች ናቸው።*

*የመዝጊያ ጥያቄ*

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

   **መልስ፡-** *መልስ የለም*

# ደጋፊ 3

*አጠቃላይ ጥያቄዎች*

1. በዲያስፓራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?

   **መልስ፡-** *አልተደረገም።*

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?

   **መልስ፡-** *የፓለቲካ ውጥረት ሳይሆን ፡ የኢኮኖሚ ውጥረት ነው ዋናው። አንዳንዴ ውጥረት ይታያል ፤ በህዝቡም ላይ የሚያመጣው ጫና ይኖራል። ህዘቡ ስለኑሮ ውድነት መፍትሄ ማንን እንደሚጠይቅ*

*አያቅም ፥ የታክስ መብዛት ፥ ያንዳንድ ነገሮች መወደድ። መንግስት መፍታት ካለመቻሉ የተነሳ ውጥረቱ ወደ ሌላ አቅጣጫ ሊሄድ ይችላል። መንግስትን ስጋት ላይ የሚያደርስ የፓለቲካ ውጥረት መፍጠር የሚችሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ብዙም አይታዩም።*

3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

**መልስ፡-** *የለም። ተቃዋሚዎች እስር በርስ አይስማሙም። አንድ ደህና ከተገኘ ፡ ያንን ፓርቲ የሚያጠቁት ተቃዋሚዎች ናቸው።*

***የመግባባት ጥያቄዎች***

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

**መልስ፡-** *መንግስት ሹሞችን መቆጣጠር አለበት። እነሱ በትክክል ከሰሩ ህዝቡ ካልተቆጣ ነገሮች ይፈታሉ ፤ መንግስት ህዝቡን ማንበብ ከቻለ ተቃዋሚዎች የሚሉት ያጣሉ። አገሪቷን ለነጋዴዎች አሳልፎ መስጠት የለበትም። ቀበሌ ለድሆች መፍትሄ ነበር። ከየትም ይምጣ … ህዝቡ በቀን ሁለት ጊዜ መብላት መቻል አለበት። ነጋዴዎች ገበያውን ብቻቸውን መቆጣጠሩ ጎጂ ስለሆነ ፡ ቀበሌ ጥሩ ተፎካካሪ ይሆናል። ነጋዴው ምርት ይደብቃል። ኑዳጅ ተወደደ።*

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

**መልስ፡-** *ተፎካካሪ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ስልጣን ለመያዝ ነው ስራቸው። ውጥረቱ ሊፓለቲካቸው ይጠቅማቸዋል። በግል ኑሯቸው ግን ተቃዋሚዎች በቂ የገቢ ምንጭ ስለሌላቸው የውጥረቱ (የኑሮ ውድነት) ሰለባ ናቸው።*

***ዲያስፓራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች***

6. የምርጫ 2002 99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

**መልስ፡-** *ለፕሮፓጋንዳ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ኢህአዴግ የሚሰራውም ስራ መታየት አለበት። ኢህአዴግ የዲያስፓራውን መጥፎ ዝንባሌ ለራሱ ፕሮፓጋንዳ እየተጠቀመበት ነው።*

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፓለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፓራ ላይ ምን አይነ ት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

**መልስ፡-** *መልስ የለም*

***የተለያዩ ሰዎች ውጠርት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ኃሳፊ-ሃሳቦች***

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

**መልስ፡-** *ያስኬዳል። በምርጫ መሆን አለበት። ዝም ብሎ መንግስት የሚሆኑበት መንገድ የለም። ብዙ ተቃዋሚዎች ናቸው ያሉት (ከ96 ተቃዋሚዎች በላይ) ሁሉም ፓርላማ ቢገቡ ፓርፓማው ተቃዋሚ ብቻ ሊሆን ይችላል።*

9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፓሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

**መልስ፡-** *አላስብም። አንድ ሚኒስቴር ምንም ነገር ሊቀይር አይችልም። በአማካሪነት ቢሰራ ብዙ ነገሮችን ፣ በተለይ ብቃት ያለው ሰው ከሆነ ፣ የማሳመን ችሎታ ያለው ሰው ከሆነ፣ በአማካሪነት ቢያገለግል አቅም የመፍጠር ጉዳይ ሊሆን ይችላል።*

10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፓሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገበር ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

**መልስ፡-** *በጣም! ኢህአዴግ ውስጥ ያሉ ሰዎች ሙሰና ውስጥ ያሉ ናቸው። የፓሊሲ ችግር አይደለም ፣ የአፈጻጸም ችግር ነው። "ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል" የሚለው አስተሳሰብ ስላለ ችግር ፈጥሯል። ሙስናን ለማርገብ ህዝብ ፣ መንግስት ፣ ተቃዋሚ ተባብረው መስራት አለባቸው። አሁን ተቃዋሚዎች ሙስናን ማጋለጥ ይችሉ ነበር። ህዝቡ መብቱን እና ግዴታውን ማወቅ አለበት ፤ ህዝቡ ሊነቃ ይችላል።*

***የእውቅና ጥያቄ***

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

**መልስ፡-** *አይሰጡም። ምክንያቱም ተቃዋሚዎች ተያያዥነታቸው ከቀድሞ ስርአቶች ጋር ስለሆነ ፥ "ወያኔን መግደል ኢትዮጵያን ማዳን ነው" ብለው የሚያምኑ መሪዎች ስላሉ ፥ ወያኔን ጭራቅ ነው ብለው ይፈርጁታል። ህዝቡ ግን የኑሮ ውድነቱ እንዲቀንስ ይፈልጋል ፤ ጥሩን ጥሩ ይላል ፣ መጥፎውን መጥፎ ይላል። እውቅና መስጠቱ ውጥረት ያረግባል። ተደማጭነት ማግኘት ይቻላል። በፓሊቲክ ደረጃም ይህ ይታያል። ተቃዋሚዎች ሚዛናዊ ቢሆኑ ከመንግስትም ዘንድ የመለሳለስ ሁኔታ ይፈጥራል። አቀራረብ ወሳኝ ነው።*

***የመዝጊያ ጥያቄ***

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

**መልስ፡-** *መልስ የለም*

# ደጋፊ 4

***አጠቃላይ ጥያቄዎች***

1. በዲያስፓራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?

   **መልስ፦** *አልተደረገም*

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?

   **መልስ፦** *ከአቶ መለስ በኋላ እሳቸውን ሚተካ ሰው አልተገኘም። ክፍተት አለ። ሶስት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች መሾማቸው ያንን ያመላክታል።*

3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

   **መልስ፦** *ከውጪ ሆነህ ለመመለስ አይቻልም። የተማርነው ሰዎች የፈጠርነው ሁኔታ አለ።*
   ***የመግባባት ጥያቄዎች***

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፦** *ተቃዋሚዎች ናቸው ኢህአዴግን አሁን ያለበት ደረጃ ያደረሱት።*

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፦** *1ኛ. በትጥቅ ትግል አላምንም። የድሃ ልጅ ነው ሚሞተው። በሰላማዊ መንገድ ነው ማምነው። 2ኛ. ህገመንግስቱን እንከተል። ሚቀየረው በአመጽ ሳይሆን በንግግር ነው። በህገመንግስት የሚሄድ መሆን አለበት። 3ኛ. ግልጽ ፕሮግራም መኖር አለበት። ቅንጅት ስምንት ነጥብ አለን ይል ነበር። እንደዚያ አይነት ነገር ያስፈልጋል። መፈክር ስሜታዊ ነገር ነው። 4ኛ. ሌሎች ከልሎች ምን ይፈልጋሉ። ተቃዋሚዎች ክልሎች ሄደው ማስተማር አለባቸው።*

***ዲያስፓራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች***

6. የምርጫ 2002 99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

   **መልስ፦** *ለተቃዋሚዎች አልጠቀመም። 1997 ተቃዋሚዎች አጥፍተዋል። ኢህአዴግ 99.6% ወንበር ማሸነፉን ተቃውሜ ነበር። ኢህአዴግ የተቋም ግንባታ ላይ ማተኮር አለበት።*

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፓለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፓራ ላይ ምን አይነ ት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

   **መልስ፦** *መልስ የለም።*

*የተለያዩ ሰዎች ውጤርት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ንደፈ-ሃሳቦች*

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፖለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

**መልስ፡-** *ማንን ከሚወክሉ ተቃዋሚዎች ጋር? ተቃዋሚዎች ማን ናቸው? ማንን ይወክላሉ? መጨመራቸው ምን ለውጥ ያመጣል? ለልማታዊ መንግስት ምን አይነት አስተዋጽኦ ያመጣል?*

9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፖሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፖለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

**መልስ፡-** *በራሱ ችግር አይደለም። የሚገቡት ሰዎች ፕሮግራም ምንድን ነው? ትንሽ ውጥረቶችን ሊቀንስ ይችላል። ግን ምንድን ነው ፕሮግራማቸው? ገና ከዘር እና ከሃይማኖት አልወጣንም። ከኢህአዴግ ጋር የሚጣጣም ርእዮታለም መሆን አለበት።*

10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፖሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገበር ለፖለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

**መልስ፡-** *ከሙሰና የተነሳ የታሰሩ ሰዎች አሉ። ተቃዋሚዎች ግን አሁንም በዘር ይንቃሉ። ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እውቅና አይሰጡም።*

*የእውቅና ጥያቄ*

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

**መልስ፡-** *የህወሃትን መስዋዕትነት አለማክበር ከህወሃት ጋር ለመቀራረብ እንቅፋት ይሆናል። ተቃዋሚዎች የመለስን መሞት በሚመለከት የተጠቀሙት ቃል ጎጂ ነበር። ተቃዋሚዎች እውቅና መስጠት አለባቸው። ሰብዓዊነት ያስፈልጋል።*

*የመዝጊያ ጥያቄ*

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

**መልስ፡-** *"ተቃዋሚዎች ንጹህ የሆኑ ሰዎች አሉ። ሁሉም መጥፎ ናቸው ማለቴ አይደለም።"*

# ደጋፊ 5

## *አጠቃላይ ጥያቄዎች*

1. በዲያስፓራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?

   **መልስ፡-** *አልተደረገም።*

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?

   **መልስ፡-** *ውጥረት አለ።*

3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

   **መልስ፡-** *በተቃዋሚዎች እና በመንግስት መካከል አለመስማማት አለ።*

## *የመግባባት ጥያቄዎች*

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፡-** *ዋናው የውጥረት ምክንያት ተቃዋሚዎች ናቸው።*

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፡-** *ተቃዋሚዎች በሂደት ማለፍ አለባቸው። ዋናው የውጥረት ምክንያት ተቃዋሚዎች ናቸው። ተቃዋሚዎች 'መንግስት መውረድ አለበት' ነው አቋማቸው። ሌላ አማራጭ መፍጠር አለባቸው። አቋራጭ ይፈልጋሉ። ተሰሚነትህ ህዝብን ያቀፈ ሲሆን ነው ፥ የተቃዋሚዎችን የሚመሩት ግነ ዲያስፓራ ያሉ ናቸው።*

## *ዲያስፓራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች*

6. የምርጫ 2002 99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

   **መልስ፡-** *ለውጥ አላመጣም። ግን የኢሳት ሰሚ ጨምሯል።*

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፓለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፓራ ላይ ምን አይነ ት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

**መልስ፡-** *መልስ የለም*

*የተለያዩ ሰዎች ውጠርት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ንደፈ-ሃሳቦች*

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፖለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *ውጥረትን አያረግብም። ተቃዋሚዎች ፡ ያንን መንግስት ማውረድ ይፈልጋሉ። ጊዜያዊ መፍትሄ ነው። የርዕዮትአለም ልዩነቱ ሰፊ ስለሆነ ጊዜያዊ መፍትሄ ብቻ ነው።*

9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፖሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፖለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *እንደ ሃሳብ ጥሩ ነገር ነው። እውቀት ያላቸው ሰዎች አሉ። ዋናው ነገር ተቃዋሚዎች ችግራቸው ምንድን ነው? ኢጋጣሚ ከተገኘ ግን የተቃዋሚ ሰዎችን ማሳተፉ ተገቢ ነው። የተቃዋሚዎች ታማኝነት አጠያያቂ ሊሆን ይችላል ፥ ህኢዴግን አደጋ ላይ ሊጥለው ይችላል።*

10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፖሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገበር ለፖለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *ፖሊሲ አማራጮቻቸው ቢተገበሩም ሌላ ሰበብ አያጡም።*

*የእውቅና ጥያቄ*

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

   **መልስ፡-** *እውቅና አይሰጡትም ፥ ያረክሱታል። እኔ ጣሊያንን በመዋጋት በአድዋ የተሰዉትን ሁሉ ኢትዮጵያውያን አከብራለሁ። ህወሃት/ኢህአዴግ የከፈለውን መስዋዕትነት አለማክበር ውጥረቱን ያከረዋል። የማያከብሩበት ዋናው ምክንያት ግን ጥላቻ ነው። ሌላው ግን የፖለቲካ ታክቲክ ነው። ተቃዋሚዎች መስዋዕትነቱን ቢያከብሩት የህወሃት ደጋፊዎች ጥሩ ስሜት ሊሰማቸው ይችላል። መንግስት ተቃዋሚዎችን ለማቅረብ ይረዳዋል።*

*የመዝጊያ ጥያቄ*

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

   **መልስ፡-** "ምርጫ 97 ውጤት ቢወስዱ ኖሮ ፡ ብዙ ደጋፊዎችን ያገኙ ነበር።"

# ደጋፊ 6

*አጠቃላይ ጥያቄዎች*

1. በዲያስፓራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?

   **መልስ፦** *አልተደረገም።*

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?

   **መልስ፦** *አለ። ከዚህ መንግስት ጋር ንክኪ የነበራቸው ፥ ታሪክ ያላቸው ግለሰቦች የውጥረቱ ተሳታፊዎች ናቸው።*

3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

   **መልስ፦** *አለመግባበት አለ። መግባባት የሚፈጠር ግን አይመስለኝም። "ኢትዮጵያዊነት" በአምቢተኝነት  የተቀረጸ ማንነት ነው። ማንነታችን ሚገለጸው እና ስሜታችን የሚደምቀው ጽንፈኛ ስንሆን  ነው። ወታደራዊ የሆነ ምንነት ነው።*

*የመግባባት ጥያቄዎች*

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፦** *አገር ውስጥ ያለው ሁኔታ በውጭ አገር ላለው ጽንፈኝነት የሚጫወተው ሚና አለ። ሁለት ቡድኖች አሉ፦ ጥላቻ ያላቸው እና ዴሞክራሲ ሚፈልጉ። ኢህአዴግ ጥላቻ ሚያራግቡት ላይ ነው ሚያተኩረው ፥ ትኩረት ማድረግ ያለበት ዴሞክራሲ የሚፈልጉት ላይ ማተኮር አለበት። ሚዲያ ፥ ፓርላመት ላይ የኢህአዴግ ያለው የበላይነት ሚዛናዊ አለመሆኑን ያሳያል። ኢህአዴግ እንደ ኢዴፓ ያሉ ፓርቲዎችን እንዲጠናከሩ ቢያደርግ ተገቢ ነው።*

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፦** *ተቃዋሚዎች መንግስት ብዙ ሃይል አለው ብለው ያምናሉ። አማራጭ ድምጽ መኖር አለበት። ጤነኛ ህብረተሰብ ለመሆን ሌላ አማራጭ ድምጽ መሰማት አለበት። ተቃዋሚዎች ኢህአዴግን "ኢትዮጵያዊ አይደለህም" ፥ "አገር አስገንጣይ ናችሁ" የሚለውን ንግግራቸውን ማቆም አለባቸው። የሕወሃትን እንደ ጠላት ማየት አለ። ወደፊት ያለው ላይ ነው ፓርቲዎች ማተኮር ያለባቸው።*

*ዲያስፓራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች*

6. የምርጫ 2002 99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

**መልስ፡-** *ግንቦት7 ፡ ኢሳት እና ሌሎች ለኢህአዴግ አደጋ አይደሉም። ሁከት ለመፍጠር አቅሙ የላቸውም። አገር ውስጥ ሁከት ከተነሳ ግን ሊያጋግሉት ይችላሉ።*

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፓለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፓራ ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

   **መልስ፡-** *አገር ውስጥ ችግር ቢፈጠር ሊያጋግሉ የሚችሉ ሃይሎችን ማዳከም ይቻላል።*

***የተለያዩ ሰዎች ውጠርት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ንድፈ-ሃሳቦች***

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *ለጊዜያዊ መፍትሄ ጥሩ ነው ፥ ግን አማራጭ ድምጽ ያስፈልጋል። የረዥም ጊዜ አማራጭ ያስፈልጋል። ጥምረቱ የሚያቆምበትን መስፈርት ማበጀት ያስፈልጋል።*

9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፓሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *ውጥረትን ለማብረድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውስጥ ተቃዋሚዎችን ማጠቃለሉ ጊዜያዊ መፍትሄ ሊሆን ይችላል።*

10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፓሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገብር ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

    **መልስ፡-** *ውጥረትን ለማብረድ ሊረዳ ይችል ይሆናል።*

***የእውቅና ጥያቄ***

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

    **መልስ፡-** *እውቅና አይሰጡም።*

***የመዝጊያ ጥያቄ***

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

    **መልስ፡-** *መልስ የለም።*

# መልሶች፡- የህጋዊ ተቃዋሚ ደጋፊዎች

# ተቃዋሚ 1

***አጠቃላይ ጥያቄዎች***

1. በዲያስፓራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?

   **መልስ፡-** *አልተደረገም።*

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?

   **መልስ፡-** *በጣም አለ። የስርዓቱ መስራቾችና ደጋፊዎቹ ሚያራምዱት ውጥረት አለ ፥ ምዕራባውያን ያጠናክሩታል።*

3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

   **መልስ፡-** *አዎ። የስርዓቱ መስራቾች ፡ ደጋፊዎቹም ሚያራምዱት። ምዕራባውያን ያጠናክሩታል።*

***የመግባባት ጥያቄዎች***

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፡-** *ህዝቡን ባህልና ወግ ፤ ጥያቄ ማዳመጥ። ራሱ ህገመንግስቱ አለመተማመንን ፈጥሯል። ህገመንግስቱን ለውይይት ማቅረብ።*

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፡-** *በሰላማዊ መንገድ መንቀሳቀስ ፥ ከህዝቡ ጋራ ዉይይት ማድረግ አለባቸው።*

***ዲያስፓራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች***

6. የምርጫ 2002 99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

   **መልስ፡-** *ምንም ለውጥ አላመጣም። ምንአልባት የሰላማዊ ትግል ትተው ወደ ትጥቅ ትግሉ እንዲገፉ ሊደርጓል።*

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፓለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፓራ ላይ ምን አይነ ት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

   **መልስ፡-** *መልስ የለም።*

***የተለያዩ ሰዎች ውጠርት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ንደፈ-ሃሳቦች***

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *የሽግግር መንግስት አይነት ባህሪ ካለው መፍትሄ ነው ብዬ አስባለሁ።ከፍተኛ ውጥረት ሚያመጣው ፡ የጥምረት መንግስት ወደ ምርጫ ሚያመራ ከሆነ ነው።*

9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፓሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *መፍትሄ የለውም። የዘመድ አዝማድ ስብስብ ሆኗል። አማካሪነት ለውጥ አያመጣም። ስልጣን ሊኖራቸው አይችልም።*

10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፓሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገብር ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *ችግሩ እዛ ጋር አይደለም። የኢትዮጵያ የሉአላዊነት ጥያቄ እስካለ ድረስ ፥ የስልጣን ክፍፍል አለመኖር ፥ የፌደራሊዝም ጥያቄ ፥ አንቀጽ 39 ችግር ፥ ህገመንግስቱ ለብሄረተሰቦች ነው ሉአላዊነት የሚሰጠው ፤ ለኢትዮጵያዊነት አይደለም።*

***የእውቅና ጥያቄ***

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

   **መልስ፡-** *አያከብሩትም። ለምን? የህወሃት ሰዎች መስዋዕትነት ለመገንጠል ነው። የመስዋዕትነቱ አላማው ለኢትዮጵያዊነት አይደለም። ትግራይን የበላይ ለማድረግ ነው።*

***የመዝጊያ ጥያቄ***

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

   **መልስ፡-** *"ህገ መንግስቱ ዋናው የውጥረት መነሻ ነው። የኢትዮጵያዊነትን ዜግነት አጥፍቷል።"*

# ተቃዋሚ 2

## *አጠቃላይ ጥያቄዎች*

1. በዲያስፓራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?

   **መልስ:-** *አልተደረገም።*

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?

   **መልስ:-** *አዎ ፤ በጣም አለ። የፓለቲካ ባህሪያችን የጸነፈና ጥላቻ የተሞላ ነው።*

3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

   **መልስ:-** *አዎ። ግንባር ቀደምነት ፓለቲካው እንዲካረር ሚፈልገው ኢህአዴግ ነው። ከተቃዋሚዎች አክራሪ የት ነው ብትለኝ ዲያስፓራ ያለው ነው። በመሪነት ደረጃም ፡ የአደባባይ ሰዎችም አሉ። አንዳንዶች የፓለቲካው ሜዳ የኢትዮጵያን ህዝብ ችግር ሊፈታ እንደማይችል ያምናሉ ፤ ስለዚህ ሁሌ ወደግንባር የሚመጡት ሰዎች አክራሪና ጽንፈኛ ሰዎች ናቸው። እንዲካረር ሚፈልጉት አንዳንዶቹ ሰዎች የግል ችግር ያላቸው ናቸው።*

## *የመግባባት ጥያቄዎች*

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ:-** *ለኢህአዴግ ውጥረቱ ለረጅም ጊዜ የጠቀማቸው ስትራቴጂ ነው። እርስ በርሳችን ያለን ግንኙነት ነው ኢህአዴግ እንዲንቀን ያደረገው።*

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ:-** *የተለዬ አመለካከት ያለው ኢትዮጵያውያን ጋር አንድ ላይ መስራት አለብን። አብረን እስካልሰራን ድረስ ኢህአዴግ አያከብረንም።*

## *ዲያስፓራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች*

6. የምርጫ 2002
   99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያ ዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

   **መልስ:-** *እርግጠኛ ለመሆን ያስቸግረኛል። ዲያስፓራ ባህል እውቅናን አይሰጥም ፤ ባህሉ የነበረ ነው። ግን መሳሪያ ሰጣቸው። ውጤቱ ለኢህአዴግ ጎድቶታል ፤ ውጤቱ ገጽታውን ጎድቶታል። ከአለም ህዝብ ጋር ያለውን ግንኙነት ጎድቶታል።*

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፖለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፖራ ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

**መልስ፡-** *አገር ውስጥ ያለው መግባባት ቢፈጠር ዲያስፖራ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ ጤነኛ ይሆናል። ዲያስፖራ ያሉትም ድርጅቶች አገር ውስጥ ያለውን ነገር ይጠቀሙበታል። የዲያስፖራ ፖለቲካ ባህል ይቀየራል።*

### *የተለያዩ ሰዎች ውጠርት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ንድፈ-ሃሳቦች*

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፖለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

**መልስ፡-** *በዚህ ሃሳብ አልስማማም። ውድድሩ በጣም ስለተካረረ ነው ውጥረት የተፈጠረው። የጥምረት መንግስት ስትፈጠር ፡ ውድድሩ አይቀርም። እንዲያውም ያኔ ነገሩ ይበልጥ ሊካረር ይችላል። ጥምረት መፍጠር ኢህአዴግ ከፈለገ ፡ ተቋሞችን ነጻ ማድረጉ የተሻለ አማራጭ ነው የሚሻለው። ሌኒናዊ ሃሳብ ነው ፤ አላማው ጊዜያዊ እንጂ ዘለቄታዊ አይደለም። ያልተረጋጋ ጥምረት ነው። ህዝብ ያልወከለው ጽንፈኛ ቡድን ወደ ስልጣን ላይ ሊመጣም ይችላል።*

9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፖሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፖለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

**መልስ፡-** *ዴሞክራሲ ባልተመሰረታቸው አገሮች ይሄ ጥቅም አለው ፤ ከፖለቲካ ውጪ የሆነ ሰው ማጠቃለል ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ብቃት ያላቸውን ሰዎች ማሳተፉ ጥሩ ነው። ግን ይሄ ነገር በጣም ትልቅ ስልጣን ነው። በጎ ስሜት ሊፈጥር ይችላል ፤ ግን ይሄ ነገር ኢህአዴግ "እየደከመ" ነው ብለው ሰዎች እንዲያዩት ሊያደርግም ይችላል። ሌላው ከኢህአዴግ ሰዎች "እኛ እያለን ለምን ሌሎችን?" የሚል ተቃውሞ ይነሳል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሄንን ለማድረግ የሚያስችል የፖለቲካ አቅም የላቸውም። ከዚህ ሁሉ ምርጫ ቦርድንና ፍርድ ቤቶችን ከፖለቲካ ነጻ ሆነው ማቋቋም ይሻላል።*

10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፖሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገበር ለፖለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

**መልስ፡-** ምርጫ ቦርድንና ፍርድ ቤቶችን ከፖለቲካ ነጻ ሆነው ማቋቋም ይሻላል።

### *የእውቅና ጥያቄ*

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

**መልስ፡-** *ህወሃት መስዋዕትነት የከፈለ ድርጅት ነው። በትጥቅ ትግል ማሸነፋቸውን እውቅና እሰጣለሁ። ብልህ መሪዎች ስለነበሩ ነው ያሸነፉት። ከህወሃት መማር አለብን። ተቃዋሚዎች ለህወሃት*

*መስዋዕትነት ዕውቅና ቢሰጡ ለትግራይ ህዝብ ጠቃሚ ነው ፤ ብዙ መከራ ያለፈ ህዝብ ነው ፡ ያንን መቀበል ከህዝቡ ጋር ግንኙነትን ሊያሻሽል ይችላል።*

***የመዝጊያ ጥያቄ***

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

**መልስ፡-** *"ትኩረት መስጠት ምፈልገው ፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ተቃዋሚዎች መጠናከር አለባቸው። ፉክክር ነው ለውጥ የሚያመጣው። ኢህአዴግን ለራሱ ብሎ እንደ ጨው እንዲጣፍጥ ያስገድደዋል።"*

# ተቃዋሚ 3

***አጠቃላይ ጥያቄዎች***

1. በዲያስፓራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?

**መልስ፡-** *አልተደረገም።*

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?

**መልስ፡-** *በሚገባ ውጥረት አለ። የፓለቲካ ፥ ማህበራዊ ፥ የኢኮኖሚ። የፓለቲካው ውጥረት የቆየ ነው። ጥያቄ ከተነሳ ብዙ ነገር ማንሳት ይጠይቃል። የዴሞክራሲ ስርዓት ለመፍጠር ከተደረገው ትግል ጋር ይገናኛል። ሰዎች የፓለቲካ አስተሳሰባቸውን የማራመድ ነጻነት ከማጣታቸው የተነሳ ጭምር ነው። የውጥረቱ ተሳታፊዎች የፓለቲካ ሊሂቃኑ ነው። የተማረው ክፍል ሊሂቃኑ ፥ በተለይ የምሁራኑ ሊሂቃን።*

3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

**መልስ፡-** *አለመግባባት አለ።*

***የመግባባት ጥያቄዎች***

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

**መልስ፡-** *ድርጅቱ (ኢህአዴግ) አለ ብዬ አላምንም ፥ ህወሃት ነው ያለው። መግባባት መፍጠር የሚችለው ህወሃት ነው። ተፈጥሯቸው ይህንን ይፈቅዳል ብዬ አላምንም። ብሄራዊ መግባባት ለህወሃት ከጉዳቱ ይልቅ ጥቅሙ ከፍተኛ ነው። ለታሪክ አስቀምጠው የሚያልፉትም ነገር ትልቅ ነገር ይሆናል። ወኔ አላቸው ወይ የሚለው አጠያያቂ ነው። እምነታቸውም አይመስለኝም።*

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

**መልስ፡-** *ተቃዋሚዎች ለመግባባት ይሰራሉ። ሁሉም ድርጅቶች ከስርዓቱ ጋር ተቀምጠው መስራቱ አማራጭ እንደሌለው ያምናሉ።*

### *ዲያስፓራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች*

6. የምርጫ 2002 99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

**መልስ፡-** *ዲያስፓራ ወደ ትጥቅ ትግል ድጋፍ የገባው የቅንጅት መሪዎች ከተፈቱ በኋላ ነው። ዲያስፓራው ምርጫ 2002ን ላይ መሳተፍን አይደግፍም ነበር። ዲያስፓራው ከሚናው ባለፈ ነው የሚጫወተው።*

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፓለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፓራ ላይ ምን አይነ ት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

**መልስ፡-** *በዲያስፓራ ያለው ነገር ይቀየራል።*

### *የተለያዩ ሰዎች ውጠርት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ንድፈ-ሃሳቦች*

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

**መልስ፡-** *የሚያጓጓ ነው። የፓለቲካች ውጥረት አንድ ቦታ ላይ መቆም አለበት።*

9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፓሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

**መልስ፡-** *ፓሊሲ ላይ ሳይሆን አስፈጻሚው ነው ወሳኙ። ውጥረቶችን በማርገብ ላይ ግን ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።*

10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፓሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገብር ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

**መልስ፡-** *ነጻ ፍርድ ቤት ፣ ነጻ ምርጫ ቦርድ ... ውጥረት ለማርገብ ዋና ነጥቦች ናቸው። መሰረታዊ መብቶች መከበር ወሳኝ ጥያቄዎች ናቸው። እነዚህ ጥያቄዎች ናቸው ውጥረት የሚያባብሱት።*

### *የእውቅና ጥያቄ*

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

**መልስ፡-** *መስዋዕትነታቸው ዋጋ እንዳይኖረው ያደረገው ህወሃት ነው። "መስዋዕትነታችሁ እኛን ለማጥፋት ነው ወይ?" የሚል ጥያቄ ነው ከተቃዋሚዎች የሚያስነሳው። ህወሃት አዲስ አበባን*

*ሲቆጣጠር የነበረውን ህዝብ ድጋፍ አጥቷል። ህወሃትንና ህዝብን መለየት፡- ህወሃት ከትግራይ ህዝብ ይውጣ እንጂ የትግራይ ህዝብ ጠበቃ አይደለም። አምባገነኖች ህዝብ አይደግፋቸውም። እውቅና መንሳቱ የፓለቲካ ታክቲክ ነው የሚለውን አልቀበልም።*

***የመዝጊያ ጥያቄ***

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

**መልስ፡-** *ብሄራዊ መግባባት ሲነሳ ብሄራዊ መግባበትን አንቀበልም የሚሉ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ግን መግባበት መፍጠሩ የገዢው ፓርቲ ሃላፊነት ነው ፥ በገዢው ፓርቲ እጅ ውስጥ ነው። ብሄራዊ መግባባት ነው ዋናው መፍትሄ።*

# ተቃዋሚ 4

***አጠቃላይ ጥያቄዎች***

1. በዲያስፓራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?

**መልስ፡-** *አልተደረገም።*

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?

**መልስ፡-** *አዎን አለ። የዴሞክራቲክ ኤንቫይሮመነት ስለሌለ ውጥረት አለ ፤ ምርጫ ስለሌላ። ታሪክ ያለው ጉዳይም ጭምር ነው። ቁርሾ ያላቸው ናቸው። በማክረር ደረጃ ብዙ አሉ። ስልጣን ላይ ያሉት መሪዎች ምንም አይነት የማርገብ ጥረት አላደረጉም። ግንዛቤያቸው ኮሚኒስት በመሆኑ ሌሎችን ለማንሸራሸር ቦታ ማይሰጥ ነው። ኳሱን ያለው ፡ ሜዳውም ያለው በገዢው ፓርቲ ነው።*

3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

**መልስ፡-** *አለመግባባት አለ።*

***የመግባባት ጥያቄዎች***

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

**መልስ፡-** *ገዢው ፓርቲ ነጻ የሆነ ምህዳር መፍጠር ፤ ተቃዋሚዎችን በጠላትነት መፍረጅ ማቆም አለበት። መሰረታዊ መብቶችን ማክበር አለበት። ተቃዋሚዎችን ይንቃል። የህዝቡን ጥያቄ መመለስ አለበት፡- የመናገር ነጻነት የለም። ገዢው ፓርቲ ክፍት የሆነ የሃሳብ ልውውጥ (dialogue) መድረክ መፍጠር አለበት።*

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

**መልስ፡-** *ገዢውን ፓርቲ ያሉትን እሴቶች ማክበር። አግባብ ባለው መንገድ መሳተፍ። ህዝቡን ማንቃትና ማደራጀት። ማስፈራራት ማቆም አለባቸው።*

*ዲያስፓራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች*

6. የምርጫ 2002 99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

**መልስ፡-** *ትልቅ ተጽዕኖ አድርጓል። የዲያስፓራን ድጋፉን ሸርሽሮ ወደነ ግንቦት7/አነግ/ኢሳት ዲያስፓራው እንዲያዘነብል አድርጓል። ኢህአዴግ ወደ አዲስ አበባ ሲገባ የነበረው አይነት የሃሳብ ነጻነት ቢፈቅድና የዴሞክራሲያዊ ምህዳር ቢፈጥር የዲያስፓራን ጽንፈኝነት መሸርሸር ይቻላል። ዲያስፓራ ሚፈልገው ዴሞክራሲያዊ መብቶች (የመናገር መበት ...) መከበር ነው።*

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፓለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፓራ ላይ ምን አይነ ት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

**መልስ፡-** *ዲያስፓራ ሚፈልገው ዴሞክራሲያዊ መብቶች (የመናገር መበት ...) መከበር ነው።*

*የተለያዩ ሰዎች ውጠርት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ንድፈ-ሃሳቦች*

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

**መልስ፡-** *በተወሰነ ደረጃ ውጥረቱን ሊያረግበው ይችላል። የዴሞክራሲያዊ መብቶችም አብረው መምጣት አለባቸው።*

9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፓሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

**መልስ፡-** *ሰዎችን መቀያየር መፍትሄ ሊሆን አይችልም። የፓሊሲ ጉዳይ ነው ዋናው። ተቃዋሚዎችን ሊያስደስት ይችላል ግን ዋናው ችግራችን የዴሞክራሲያዊ መብቶች ጉዳይ ነው።*

10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፓሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገብር ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

**መልስ፡-** *ኢኮኖሚው ላይ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። ዋናኙ የሚያቀርቧቸው ጥራት ፖሊሲ ነው። የአፈጻጸም ችግር ከፓሊሲ አቀራረጽ ጋር የተገናኘ ነው። ፓለቲካ እና ኢኮኖሚ አይነጣጠልም። መንግስት እና ፓርቲ በኢኮኖሚ ውስጥ ተሳትፎ እስካለ ድረስ ችግሮች ይቀጥላሉ።*

*የእውቅና ጥያቄ*

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

**መልስ፡-** *ውጤቱ አውቅና እንዳይሰጡ ምክንያት ነው። መስዋዕትነት አልከፈላችሁም የሚል የለም። ህወሃትን እና የትግራይን ህዝብ መለየቱ የትግራይን ህዝብ አያስከፋውም። መስዋዕት የከፈሉት ኢትዮጵያውያን ናቸው። መስዋዕትነቱ ለኢትዮጵያ ነው የከፈሉት ብዬ ነው ማምነው። ደርግን ማውገዝ የኢትዮጵያን ሰራዊት ማውገዝ እንዳልሆነው ሁሉ ማለት ነው። በቀይ ሽብር ከ100ሺ በላይ ሰዎች ተሰውተዋል። ህወሃት አሁን በሚያደርገው ድርጊት ነው የሚጠየቀው። ግለሰቦች መስዋእትነቱን ሊያጣጥሉ ይችላሉ ፡ ድርጅቶች መስዋእትነቱን አይክዱም።*

***የመዝጊያ ጥያቄ***

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

**መልስ፡-** *አሁን ባለው ሁኔታ አገሪቱ ወደ አደገኛ ሁኔታ እየሄደች ነው ፤ አማጺያን ብዛት ጨምረዋል ፤ ብሄራዊ መግባባት ነው ከአደገኛ ሁኔታ ሊያድነን የሚችለው።*

# ተቃዋሚ 5

***አጠቃላይ ጥያቄዎች***

1. በዲያስፖራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?

**መልስ፡-** *አልተደረገም።*

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?

**መልስ፡-** *ውጥረት አለ። የኑሮ ውድነት ፡ የጎሳ ፓለቲካ ክፍፍል ፡ የታመቁ ችግሮች አሉ። ተጠቃሚዎቹ ጥቂቶች ናቸው። ስርዓቱ ዋናው ተሳታፊ ነው። ውጥረቱን የማርገብ አቅምም አለው። የተቃዋሚ ፓርቲዎች የማጋለጥ ስራ ይሰራሉ። ግን ለውጥረቱ መንስኤ ተቃዋሚዎች ናቸው ብዬ አላምንም። የውጥረቱ ዋና ምንስዔ የህዝብ ብሶት ነው። ትልቁ ውጥረት የህዝብ ውጥረት ነው።*

3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

**መልስ፡-** *አለመግባባት አለ።*

***የመግባባት ጥያቄዎች***

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

**መልስ፡-** *ለመግባባት ኢህአዴግ ውስጥ ነው ትልቁ ቁልፍ ያለው። እስረኛ መፍታት ፡ ከሌሎች ጋር መስማማት ወዘተ ማድረግ ይችላል። ያለመግባባቱ የስልጣን ጥያቄ ነው። በምርጫ ይወሰን ፥ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ይፈጠር። መግባባት ያስፈልገናል።*

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

**መልስ፡-** *ያልከረረ መንገድ።*

***ዲያስፓራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች***

6. የምርጫ 2002 99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

   **መልስ፡-** *ዲያስፓራ አብዛኛው ዝምተኛው ነው። ባለፉት 2 ዓመታት ድጋፍ የማድረጉ ሁኔታ ፡ ጨምሯል።*

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፓለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፓራ ላይ ምን አይነ ት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

   **መልስ፡-** *አገር ውስጥ ያለው ተቃዋሚ ምንም ተጽዕኖ ባይደረግበት ፡ ውጭ ያለው ጉዳይ ይረግባል። አገር ቤት ፍትህ ካለ ውጭ ያለው ነገር ወደ ልማት ላይ ያተኩራል።*

***የተለያዩ ሰዎች ውጠርት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ንድፈ-ሃሳቦች***

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *በምርጫ ከሆነ ትክክል ነው። ዘለቄታዊ መፍትሄ ነው ብዬ አላምንም።*

9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፓሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *ለሽግግር ጊዜ ሊሆን ይችላል።*

10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፓሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገብር ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

    **መልስ፡-** *ውጥረትን ለማርገብ ይጠቅማሉ።*

***የእውቅና ጥያቄ***

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

    **መልስ፡-** *የፓለቲካ ስልት ነው። የመስዋዕትነትነቱ ውጤት እንጂ መስዋዕትነቱ ዋጋ ላይ አይደለም ችግሩ። እውቅና መንሳቱ ግን የህወሃት ስሜታቸውን ማሻከሩ አይቀርም። ግን ህወሃት እየተቀየረ ነው ፤ የትጥቅ ትግሉ ትውልድ እያለፈ ነው። አዲሱ ካድሬ ግድ የለውም።ተቃዋሚዎች በሰብዓዊነት ደረጃ ክብር መስጠት አለባቸው። እውቅና መስጠቱ ተቃዋሚዎች አያቅታቸውም።*

***የመዝጊያ ጥያቄ***

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

**መልስ፡-** *መልስ የለም።*

# ተቃዋሚ 6

***አጠቃላይ ጥያቄዎች***

1. በዲያስፓራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?

   **መልስ፡-** *በዲያስፓራ ስለ ብሄራዊ መግባባት ውይይት አልተነሳም። የአጸፋ መልስ ነው ያለው።*

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?

   **መልስ፡-** *አዎ። በህዝቡ እና በወያኔ መካከል ፡ በወያኔ ውስጥም ውጥረት አለ። በተቃዋሚውም ውስጥ ውጥረት አለ። የገዢው ፓርቲ አምባገነናዊ ባህሪ የውጥረቱ ምንስዔ ነው።*

3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

   **መልስ፡-** *አዎን አለ።*

***የመግባባት ጥያቄዎች***

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፡-** *ከገዢው ፓርቲ መልካም ፈቃድ መምጣት አለበት ፤ በብት መጣስ ማቆም ፤ ማያዛልቅ መሆኑን ማመን አለበት።*

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፡-** *መጀመር ያለበት ከገዢው ፓርቲ ነው። ተቃዋሚዎች ማረግ የሚችሉት ነገር ትንሽ ነው። እስረኛ መፍታት ፡ ህዝቡ እንዲሳተፍ ማድረግ። 90% የኢህአዴግ ሃላፊነት ነው። በቂ ግንዛቤ የለም ፥ በቂ የሆነ የተመቻቸወ ምህዳር የለም። ገዢው ፓርቲ ነው ተጠያቂው ፥ ለብሄራዊ መግባባት ሃሳብ አለመዳበር አንዱ ሃላፊነቱ የገዢው ፓርቲ ነው።*

***ዲያስፓራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች***

6. የምርጫ 2002
   99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያ ዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

   **መልስ፡-** *ለሰላሳ ሰዎችን ተስፋ አስቆርጧል።*

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፓለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፓራ ላይ ምን አይነ ት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

   **መልስ፡-** *መግባባቱ ዲያስፓራ ያለውን ተቃዉሞ በ80% ሊያረግበው ይችላል።*

***የተለያዩ ሰዎች ውጤርት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ንድፈ-ሃሳቦች***

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *ገዢው ፓርቲ ከህዝቡ ጋር መታረቅ አለበት ፥ እስረኛ መፍታት አለበት። ድርድር ከተቃዋሚ ጋር ማድረግ አለበት። ከዚያ በኋላ ወደ ጥምረት መንግስት መግባት ይቻላል።*

9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፓሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *የስልጣን ጉዳይ አይደለም ፤ የህዝቡ መብት መከበር አለበት። ቅድሚ ለህዝብ ፤ ከዚያ ወደ ስልጣን።*

10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፓሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገበር ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

    **መልስ፡-** *ጊዜያዊ መፍትሄ እንጂ የህዝቡ ተሳትፎ ወሳኝ ነው። የህዝቡ ይሁኝታ መከሰት አለበት። ተቋሞች ነጻና ዴሞክራሲያዊ እስካልሆኑ ድረስ ዋጋ የለውም።*

***የእውቅና ጥያቄ***

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

    **መልስ፡-** *የመስዋዕትነትነቱ ውጤት እንጂ መስዋዕትነቱ ዋጋ ላይ አይደለም ችግሩ። እነሱ ታግለው እነሱ ተጠቃሚ ሆነዋል ፥ ትግላቸው ለራሳቸው ነው። ሁሉንም ነገር የተቆጣጠሩት እነሱ ናቸው። የኢትዮጵያን ሰራዊት በሙሉ መደምሰሱ ወያኔ የሰራው ስህተት ነው። ተቃዋሚው የሰማዕታትን ክብር መስጠቱ ዋጋ አይኖረውም። በሙስና ነቅዟል። ገብሩ አስራት ፥ አስገደ ገ/ስላሴ ወዘተ የህወሃት አባል ነበሩ ፥ አሁን ግን ተቃዋሚ ሆነዋል። ህወሃት በትግራይ ህዝብ ስም ነው የሚጠቀመው እንጂ አሁን የትግራይ ህዝብ ነጻ አይደለም።*

*የመዝጊያ ጥያቄ*

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

**መልስ፦** *መልስ የለም።*

# መልሶች፦ ለዘብተኞች

*(ለዘብተኞች' ማለት ከፓርቲ ደጋፊነት ይልቅ በመርህ ላይ ሚያተኩሩ ናቸው።)*

# ለዘብተኛ 1

*አጠቃላይ ጥያቄዎች*

1. በዲያስፓራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?

   **መልስ፦** *አልተደረገም።*

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?

   **መልስ፦** *አዎን አለ።*

3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

   **መልስ፦** *በፓለቲካ ባህላችን መግባባት አልተለመደም። የጠላትነት አስተሳሰብ አለ ፥ ካልደገፍከኝ ጠላቴ ነህ የሚል።*

*የመግባባት ጥያቄዎች*

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፦** *ኢህአዴግ ለተቃዋሚዎች ስም ያወጣል (label) ፥ ተቃዋሚዎችን ኢያምንም "አገር ያጠፉሉ ስልጣን ከያዙ" ይላል። ይህን ማለቱን ማቆቆም ጠቃሚ ነው።*

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፦** *ህጋዊ ተቃዋሚዎች በዲያስፓራው ግፊት መውጣት አለባቸው። በራሳቸው በህዝቡ መመራት አለባቸው። ውጥረት ውስጥ እንዲገባ ያደረገው የዲያስፓራው አስተሳሰብ ይመስለኛል። ተቃዋሚዎች ኢህአዴግን እንገረስሳለን እንላለን።*

***ዲያስፖራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች***

6. የምርጫ 2002 99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

   **መልስ፡-** *ጠቅሟቸዋል። ኢህአዴግ ከፍርሃት የተነሳ ነው 99.6% ወንበር ያሸነፈው። ሌላ አማራጭ የሚፈልጉ ሰዎች በዝተዋል።*

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፓለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፓራ ላይ ምን አይነ ት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

   **መልስ፡-** *የዲያስፓራ ድርጅቶችና ሚዲያዎች ድጋፋቸው ይቀንሳል።*

***የተለያዩ ሰዎች ውጥርት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ንድፈ-ሃሳቦች***

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *አብረው ሊሰሩ አይችሉም። ርዮተ አለማቸው አይታረቅም።*

9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፓሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *ውጥረቱን የማርገብ አቅም አለው። የብሄራው መግባባት አላማ አብሮ መስራት መቻል ነው።*

10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፓሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገብር ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

    **መልስ፡-** *ፖሊሲያቸው ጠቃሚ እስከሆነ ድረስ ኢህአዴግ ሊጠቀምበት ይገባል።*

***የእውቅና ጥያቄ***

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

    **መልስ፡-** *መስዋዕትነታቸውን ማክበር አለብን። ህወሃት የመጣበትን መንገድ ያማላከብር ከሆነ ፡ አብሮ መስራት አይቻልም። ክብር የማንሰጥ ከሆነ ፓለቲካው ውስጥ መሳተፍ የለብንም። ተቃዋሚዎች ተጨማሪ እውቅና የመስጠት ስራ አለባቸው።*

***የመዝጊያ ጥያቄ***

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

    **መልስ፡-** *መልስ የለም።*

# ለዘብተኛ 2

***አጠቃላይ ጥያቄዎች***

1. በዲያስፓራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?

   **መልስ፡-** *ትኩረት አልተሰውም።*

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?

   **መልስ፡-** *የለም።*

3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

   **መልስ፡-** *ምንም አይነት መግባበት የለም። ተቃዋሚዎች እልህ ፣ የኢህአዴግ ተቃዋሚዎችን አለማመን። የተቃዋሚዎች ከዲያስፓራ ድጋፍ ማግኘት ተቃዋሚዎች ነጻ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል ፥ ኢህአዴግ ጋር መግባባት እንዳያገኙ ምክንያትም ሆኗል።*

***የመግባባት ጥያቄዎች***

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

*መልስ፡- ተቃዋሚዎች ከመንግስት በጀት ማግኘት አለባቸው። ያ ከሆነ ከዲያስፓራ ተጽዕኖ ነጻ ይሆናሉ።*

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፡-** *መግባባት እንዲፈጠር ተአማኝነት ማሳየት አለባቸው። ተአማኝነታቸው ዋስትና ነው። ለኢህአዴግ ዋስትና መሰጠት አለበት። ቂምበቀልና ማስፈራራት ትተው ለህዝቡ ተአማኝነት ማሳየት አለባቸው ፥ ጥሩን ጥሩ ፣ መጥፎውን መጥፎ ማለት አለባቸው።*

***ዲያስፓራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች***

6. የምርጫ 2002
   99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያ ዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

**መልስ፡-** *አገር ውስጥ ያሉትን አዳክሚቸዋል ፥ የዲያስፖራ የገንዘብ ድጋፍ ወደ ትጥቅ ትግል እና ሌሎች መንገዶች ላይ ስላተኮረ የአገር ውስጥ ፓርቲዎች በቂ የገንዘብ ድጋፍ ከዲያስፖራ እንዳያገኙ እንቅፋት ሆኖባቸዋል።*

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፓለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፖራ ላይ ምን አይነ ት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

   **መልስ፡-** *መልስ የለም።*

***የተለያዩ ሰዎች ውጠርት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ንድፈ-ሃሳቦች***

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *ነገሮችን ያባብሳል እንጂ መፍትሄ አያመጣም። እኩል ሚዛን መኖር አለበት። ሃይል መኖር አለበት። አንድ አይነት ሁኑ ማለት ማንነትን የሚያሳጣ ነው ብዬ ነው የማምነው። የሚሻለው ተቃዋሚዎች በአገር ውስጥ ሚዲያ እንዲያገኙ ማድረግ ነው።*

9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፓሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *ከተቃዋሚዎች አንድ ሰው ቢሾም የሚደርስበት ጥቃት ከፍተኛ ነው። ካሉባሊታ መውጣት አለብን። ይሄን አኳሃን ለማምጣት አስተሳሰባችን መቀየር አለበት። መግባበት ላይ ለመድረስ አስተሳሰብ እና አመለካከት መቀየር የለባት። የጥቂቶች ሆይ ሆይታ መፍትሄ ሊሆን አይችልም።*

10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፓሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገብር ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

    **መልስ፡-** *ከተቃዋሚዎች ጋር አለመቀራረቡ ለሙስና የተመቻቸ ሁኔታ ፈጥሯል። ጥሩ መፍትሄ ነው።*

***የእውቅና ጥያቄ***

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

    **መልስ፡-** *ህወሃት ብቻ አይደለም መስዋዕትነት የከፈለው ፥ ብአዴንም መስዋዕትነት ከፍሏል። ተቃዋሚዎች ግን እውቅና አልሰጡም። እውቅናን ቢሰጡ ሊያግባባቸው ይችላል። እውቅናው ለህዝቡ ነው። በህዝቡ ዘንድ ተአማኝነትን ኢያገኘ ሊሄድ ይችላል። እውቅና ስንሰጥ ራሳችንን እናሳድጋለን። የትግራ ህዝብ ህዝብ ነው ፥ ህወሃት ግን ድርጅት ነው።*

***የመዝጊያ ጥያቄ***

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

**መልስ፡-** *"ለሃገራችን ጥሩ ለውጥ እንዲመጣ አዲሱ ትውልድ በተሻለ አመለካከት ፡ አገራችንን በትምህርት እና በኢኮኖሚ ካሳደግን አገራችን በተሻለ ሁኔታ ላይ ትደርሳለች። በልማት ላይ ብንረባረብ ጥሩ ነው። የኢህዴግ ደጋፊ አይደለሁም። የሃገሬ ጉዳይ ነው ወሳኙ ለኔ። ብዙ ከፉም ደጉንም አይቻለሁ ሰምቻለሁ። አገሬ ሰልጥና እኔ ያለፍኩበትን አሰቃዊ ነገሮች አሁን ያለው ትውልድ እንዲያይ አልፈልግም።"*

# ለዘብተኛ 3

***አጠቃላይ ጥያቄዎች***

1. በዲያስፓራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?

   **መልስ፡-** *አልተረደገም።*

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?

   **መልስ፡-** *ከውጥረት ውስጥ ወጥቶ አያቅም።*

3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

   **መልስ፡-** *አለመግባባት አለ።*

***የመግባባት ጥያቄዎች***

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

**መልስ፡-** *ብዙ ነገር ይጠበቃል። የፓለቲካ ምህዳር የማጥበቁም የማላላቱም አቅም አለው።*

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፡-** *የአገሪቱን ህግ መጠበቅ አለባቸው። ከህግ ዉጪ የሚደረገውን ነገር ላይ መጠንቀቅ አለባቸው። ህግ መሰረት ስለሆነ ህጋዊነትን የጠበቀ ስራ መስራት አለባቸው። የእምነት (conviction) ፓለቲካ ነው ወይስ ስልጣን ላይ ለመውጣት ብቻ ነው ፓለቲካ ሚያራምዱት? ስልጣን ላይ ለመውጣት ህዝብ ነው ወሳኝ መሆን ያለበት።*

***ዲያስፓራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች***

6. የምርጫ 2002 99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

**መልስ፡-** *ውጪ ያለው የጠራ አመለካከት ስለሌለው ጠንካራ ተቃዋሚ አልሆነም። አገር ውስጥ የነበረው ክፍፍል ወደ ውጪ ይዞት መቷል። ኢህአዴግ ስልጣን ላይ መሆኑ ተቃዋሚዎች ሚዲያ አጥተዋል። ኢህአዴግን ሊገዳደሩ የሚችሉ በሰላማዊ መንገድ ሊያሸንፉ የሚችሉ ፡ በፓለቲካ እምነት ላይ የተመሰረተ ትግል መሆን አለበት። ለግንቦት7 እና ሌሎች ለፕሮፓጋንዳ ጠቅሟቸዋል። ኢህአዴግ በራሱ ላይ ነው ችግር የፈጠረው ፥ ኢህአዴግ ራሱን እየገደለ እና አሳታፊ ያልሆነ የፓለቲካ ድርጅት መሆኑ ግልጽ ሆኗል። ለእርዳታ ሰጪ አገሮች ኢህአዴግን ማሳጫ ሆኗቸዋል።*

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፓለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፓራ ላይ ምን አይነ ት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

   **መልስ፡-** *መልስ የለም።*

***የተለያዩ ሰዎች ውጠርት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ንድፈ-ሃሳቦች***

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *በልማት ላይ ታላቅ ተጽዕኖ ሊያመጣ ይችላል። ኢህአዴግ ወይ ማሸነፍ ወይ ተሸንፎ ተቃዋሚ መሆን ነው ያለበት። የጥምረት መንግስት ውሳኔ ለመወን አስቺጋሪ ሁኔታ ይፈጠራል። ፓሊሲ የመቅረፅ እና ውሳኔ የመወሰን ሃላፊነት በአንድ ፓርቲ (ስብስብ) ብቻ ካልሆነ ሃላፊነት የሚወስድ አይኖርም።*

9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፓሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

   **መልስ፡-** *እንደ ባለሙያ ከሆነ ፤ አሁንም ማድረግ ይችላሉ። ካልሆነ ግን የእምነት (conviction) ግጭት ይከሰታል። ስራ አይሰራም።*

10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፓሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገብር ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

    **መልስ፡-** *ቀጣይ የሆነ ሰላም እና መግባባት ሊፈጠር የሚችለው የፓለቲካ ምህዳሩ ሲሰፋ ብቻ ነው። ሰዎች ነጻነት ሊኖራቸው ይገባል። ያለበለዚያ ዘለቄታዊ የሆነ መፍትሄ ሊሆን አይችልም።*

***የእውቅና ጥያቄ***

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

    **መልስ፡-** *የህወሃት መስዋዕትነት እና እውቅና፡- ኢትዮጵያኒስቶች እና ብሄረተኞች አሉ። ብሄረተኞች እውቅና ይሰጣሉ። ኢትዮጵያኒስቶች ግን እውቅና አይሰጡም ፥ መስዋዕትነቱ አቁስሏቸዋል።*

*እውቅናው በእምነት (conviction) ደረጃ ከሆነ ሊያግባባ ይችላል። ለፓለቲካ ጥቅም ከሆነ ግን ዘለቄታዊ አይሆንም። አንዳንዶች ህወሃትን እውቅና የሚነሱት አሃዳውያንን ስላስወገደ ጭምር ነው።*

***የመዝጊያ ጥያቄ***

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

**መልስ፦** *"ፓለቲካ የመስጠትና የመቀበል ጉዳይ ነው።"*

# ለዘብተኛ 4

***አጠቃላይ ጥያቄዎች***

1. በዲያስፓራ ሚዲያዎችና መወያያ መድረኮች ስለ "ብሄራዊ መግባባት" በቂ ውይይት ተደርጓል ብለው ያስባሉ?

   **መልስ፦** *ሙከራዎች ተደርገዋል ፤ በፓለቲካዊ ፍጇታም መልኩ ተሞክሯል። ሁሉን አቀፍ ሆኖ ግን መፍትሄ ለመፍጠር አልተደረገም።*

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የፓለቲካ ውጥረት አለ ብለው ያምናሉ? ካለ ለምን?

   **መልስ፦** *አዎ። ሶስት አመለካከቶች 1) ችግሩ የብሄር ጉዳይ ነው የሚሉ 2) የኢትዮጵያ ችግር የመደብ ጭቆና ነው የሚሉ 3) የኢትዮጵያ ችግር የሁለቱ ድምር ነው። የብሄረሰብ ብዛት ባለበት አገሮች ከማህበረሰብ እድገት ሂደት ጋር የሚገኙ ችግሮች ናቸው። የመደቡም ጉዳይ የሚዛናዊ የሃብት ክፍፍል አለመኖሩ ነው።*

3. የፓለቲካ አለመግባባት አለ ብለው ያምናሉ? ከሌለ ለምን የለም?

   **መልስ፦** *ያለፉት 50 ዓመት የሚያሳየው አለመግባበት መኖሩን ያሳያል። ደርግ የመደብ ጭቆናን ለመፍታት ሞከረ። ብሄረተኞች አመጹ። ተቀራርቦ የመወያየት መፍታት ባህል ስለሌለ።*

***የመግባባት ጥያቄዎች***

4. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከኢህአዴግ ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፦** *ችግሮቻችን መፈታት የሚችለው የብሄር እና የመደብን ችግር የሚፈታ በውይይት የሚፈጠር መፍትሄ መፈለግ አለበት። ያሸነፈው ሃሳብ ብቻ ከወጣ ፡ ሌላው ያምጻል።*

5. የፓለቲካ መግባባት ለመፍጠር ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ምን ይጠብቃሉ?

   **መልስ፦** *የፓለቲካ ምህዳሩ ጠቧል ግን ማድረግ የሚችሉት ህዝባዊ አመኔታ መገንባት ነው።*

***ዲያስፓራን ሚመለከቱ ጥያቄዎች***

6. የምርጫ 2002 99.6% የፓርላማ ወንበሮች የገዢው ፓርቲ መሆናቸው በዲያስፓራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እና ሚዲያዎች ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ አድርጓል?

   ***መልስ፡-*** *ውጪ ያሉ ተንቀሳቃሾች በምርጫ ኢህአዴግ ጋር ለመወዳደርም ፣ ለማሸነፍም ተስፋ ቆርጠዋል። ሌላ አማራጭ እየፈለጉ ነው።*

7. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች መካከል የፓለቲካ መግባባት ቢከሰት ዲያስፓራ ላይ ምን አይነ ት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

   ***መልስ፡-*** *ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል።*

***የተለያዩ ሰዎች ውጠርት ለማርገብ ያቀረቡዋቸው ንድፈ-ሃሳቦች***

8. በኢህአዴግ እና በህጋዊ ተቃዋሚዎች የጥምረት መንግስት ቢመሰረት ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

   ***መልስ፡-*** *አይመስለኝም። የፓለቲካ ርዕዮታቸው የሚስማሙ ከሆነ ብቻ ነው ፣ ያለዚያ የመናቆር ነገር ይበዛል።*

9. ተቃዋሚዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፓሊሲ በመቅረጽ ላይ ቢሳተፉ ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይሆናልን? ለምን?

   ***መልስ፡-*** *አሸናፊው ፓርቲ ፓሊሲ አለው። ሌላ ፓሊሲ ያለውን የፓለቲካ ተወካይ ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ማስገባት የፓሊሲ እና የፓለቲካ አስተሳሰብ ያላቸው ይጋጫሉ።*

10. ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎችን የፓሊሲ አማራጭ ተቀብሎ ቢተገብር ለፓለቲካ መግባባት መፍትሄ ይ ሆናልን? ለምን?

    ***መልስ፡-*** *የተወሰነ ጥገናዊ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። ገዢው ፓርቲ የራሱን ፓሊሲ መጠገኑ በራሱ ተመሳሳይ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል።*

***የእውቅና ጥያቄ***

11. ተቃዋወሚዎች ለህወሃት/ኢህአዴግ መስዋዕትነት በቂ እውቅ ይሰጣሉን? ካልሰጡ ለምን? ቢሰጡስ ለ መግባበት ጠቃሚ ነው ብለው ያስባሉ?

    ***መልስ፡-*** *እሱ ነው ዋናው ችግሩ። በቂ የሆነ እውቅና ያለመስጠት ሁኔታ አለ። "ለዚህ ነው መስዋዕትነት የከፈሉት ወይ?" ብለው ተቃዋሚዎች ይተቻሉ።*

***የመዝጊያ ጥያቄ***

12. ሊጨምሩት ሚፈልጉት ሃሳብ አለዎት?

    ***መልስ፡-*** *"የኢትዮጵያ ምሁራን ለኢትዮጵያ ሊያደርጉት የሚችሉት ፣ ነገሮችን በውይይት የመፍታትን መንገድ ለህዝብ ለማስተማር ብሄራዊ መግባባትን ቢጠቀሙ ነው።"*

*Copyright© 2013 Yaye Abebe. All rights reserved. No part of this document may be reproduced or transmitted in any form or by any means, electronic, mechanical, photocopying, recording, or otherwise, without prior written permission of Yaye Abebe.*